የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ህዳር ፩ ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 4
Addis Ababa November 10, 2006

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፺፱ ዓ.ም.
የዲላ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ገጽ ፫ሺ፬፻፹፭

*CONTENTS*

Regulations No. 129/2006
Council of Ministers Regulations to Establish the Dilla University ....................Page 3485

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፺፱**

**የዲላ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፰ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹የዲላ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፺፱›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፡

፩. ‹‹አዋጅ›› ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ ነው፡

፪. ‹‹ቦርድ›› ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ የተመለከተው የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ቦርድ ነው ፡

፫. ‹‹ሴኔት›› ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ የተመለከተው የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ነው፡

፬. ‹‹የአካዳሚክ ሠራተኛ›› ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪(፯) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ የዩኒቨርሲቲው ሠራተኛ ነው፡

***Council of Ministers Regulations No. 129/2006***

***COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO ESTABLISH THE DILLA UNIVERSITY***

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 8 of the Higher Education Proclamation No. 351/2003.

*PART ONE*

*GENERAL*

*1.Short Title*

These Regulations may be cited as the "Dilla University Establishment Council of Ministers Regulations No. 129/2006".

2. *Definitions*

In these Regulations unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Higher Education Proclamation No. 351/2003;

2/ "Board" means the Administrative Board of the University referred to in Article 9 of these Regulations;

3/ "Senate" means the University's Senate referred to in Article 10 of these Regulations;

4/ "Academic staff" means the employee of the University as defined in Article 2(7) of the Proclamation;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,000

፭. «ድርጅት» ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ የተቋቋመው የዩኒቨርሲቲው የገቢ ማመንጫ ድርጅት ነው፤
፮. «ፈንድ» ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፭ የተቋቋመው የዩኒቨርሲቲው የገቢ ፈንድ ነው፤
፯. «ሚኒስቴር» ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው፤
፰. «ክልል» ማለት የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የዩኒቨርሲቲው መቋቋም፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር

፫. **መቋቋም**

፩. የዲላ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ «ዩኒቨርሲቲ» እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለና የሕግ ሰውነት ያለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
፪. ዩኒቨርሲቲው በሥሩ የሚከተሉትን ተቋማት፣ ፋኩልቲዎችና ትምህርት ቤቶች ያካትታል፤
ሀ) የተፈጥሮ ሳይንስ መምህራን ትምህርት ፋኩልቲ፤
ለ) የሶሻል ሳይንስና ቋንቋ መምህራን ትምህርት ፋኩልቲ፤
ሐ) የትምህርት ሳይንሶች ፋኩልቲ፤
መ) በቦርዱና በሚኒስቴሩ የሚቋቋሙ ሌሎች ፋኩልቲዎች ፣ ኮሌጆች፣ ትምህርት ቤቶችና ተቋማት ፡፡
፫. ዩኒቨርሲቲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፬. **ዓላማ**

ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤
፩. ሀገሪቱን በተለያዩ ሙያዎች ሊያገለግል የሚችል ሕገ መንግሥታዊ መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ የሚያውቅ የሠለጠነ የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት ማፍራት፤
፪. የዘር፣ የሃይማኖት፣ የፆታ፣ የፖለቲካና የመሳሰሉት ልዩነቶች የማይደረግበት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት መስጠት፤
፫. ችግር ፈቺ የሆነና የሀገሪቱን እምቅ ሀብት ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ትምህርታዊና ተቋማዊ ሥርዓት መዘርጋትና ጥናትና ምርምር ማድረግ፤
፬. ከሀገሪቱና ከክልሉ ፍላጐትና ዕድገት ጋር የተጣጣመ የከፍተኛ ትምህርትና የኅብረተሰብ አገልግሎት መስጠት፤
፭. ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ተቋማዊ ሥርዓት መዘርጋት፤
፮. በአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚመለከታቸውን አካላት ተሳትፎ ማረጋገጥ ፣ የአሳታፊነት ባህልን መፍጠርና ማሳደግ፤
፯. በሰዎች መካከል የመከባበር ፣ የመቻቻልና አብሮ የመኖር ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብትና እንዲሰርጽ ማድረግ፤
፰. የአገልግሎት ክፍያ በመቀበል የምክርና ሥልጠና አገልግሎት መስጠት፡፡

5/ "Enterprise" means the income generating enterprise of the University established under Article 20 of these Regulations;
6/ "Fund" means the income fund of the University established under Article 25 of these Regulations;
7/ "Ministry" means the Ministry of Education;
8/ "Regional State" means the State of the Southern Nations, Nationalities and Peoples.

## *PART TWO*
## *ESTABLISHEMENT, OBJECTIVES, POWERS AND DUTIES OF THE DILLA UNIVERSITY*

3. *Establishment*

1/ The Dilla University (hereinafter referred to as the "University") is hereby established as an autonomous higher education institution having its own legal personality.

2/ The University shall comprise the following institutions, faculties and schools:
a) faculty of natural science teachers' education;
b) faculty of social science teachers' education;
c) faculty of educational sciences;
d) Other faculties, colleges, schools and institutions to be established by the Board and the Ministry.

3/ The University shall be accountable to the Ministry.

4. *Objectives*

The University shall have the objectives to:
1/ produce skilled manpower in quantity and quality that understands clearly its constitutional rights and duties and that will serve the country in different professions;
2/ provide higher education services that are free from any discrimination on grounds of race, religion, sex, politics and other similar grounds;
3/ lay down problem-solving educational and institutional system that enables to utilize potential resources of the country and undertake study and research;
4/ provide higher education and community services that are compatible with the needs and development of the Country and the Regional State:
5/ lay down institutional system that ensures transparency and accountability;
6/ ensure the participation of all concerned bodies in administration decision-making process, create and promote participatory culture;
7/ develop and disseminate democratic culture of respect, tolerance and living together among the people;
8/ provide consultancy and training services on the basis of fees.

፭. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩. ፋኩሊቲዎች ፣ ኮሌጆችና ሌሎች የትምህርትና የምርምር ተቋሞች አቋቁሞ የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ማካሄድ፣
፪. የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማና ዲግሪ መስጠት እንዲሁም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰዎች የአካዳሚክ ማዕረግና ሽልማት መስጠት፣
፫. ለሀገር ዕድገት ቅድሚያ በሚሰጥባቸው መስኮች ላይ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣
፬. ሴሚናሮች፣ ዓውደ ጥናቶችና ሲምፖዚየሞችን ማዘጋጀትና ማካሄድ፣
፭. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ አቻ ዩኒቨርሲቲዎች ፣ የምርምር ተቋሞችና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አካላት ጋር ግንኙነት መመሥረት፣
፮. የማማከር፣ የልዩ ሥልጠናና ሌሎች አግባብ ያላቸው አገልግሎቶች ለኅብረተሰቡ፣ ለክልል መስተዳድሮችና ለፌዴራል መንግሥት መስጠት፣
፯. የትምህርት መጽሔቶችና ጋዜጦች ማሳተምና ማሰራጨት ፣
፰. ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢ ክፍያ ማስከፈል፣
፱. የገቢ ፈንድና የገቢ ማመንጫ ድርጅት ማቋቋምና ማስተዳደር፣
፲. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል ፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ፣
፲፩. ዓላማውን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፡፡

፮. <u>የአካዳሚና አስተዳደራዊ ነጻነትና ተጠያቂነት</u>

፩. በሕግ የተደነገጉ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ ዩኒቨርሲቲው ዕውቀትን ለመሻት፣ ለማበልጸግና ለማሠራጨት የአካዳሚክ ነፃነት ይኖረዋል፡፡
፪. ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉትን ጉዳዮች በሚመለከት አስተዳደራዊ ነፃነት ይኖረዋል፣
 ሀ) የውስጥ አደረጃጀቱን በመወሰንና በጀቱንና የሰው ኃይሉን በማስተዳደር፣
 ለ) ሥርዓተ ትምህርት በመገምገምና በማሻሻል፣
 ሐ) የምርምር ስትራቴጂ በመንደፍና በማስፈጸም፣
 መ) የትምህርት፣ የምርምርና የኅብረተሰብ አገልግሎት ኃላፊነቱን ለመወጣት ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የትብብር ግንኙነት በመፍጠር፣
 ሠ) ከዓላማው ጋር የሚሄድ የገቢ ማመንጫ ድርጅት በማቋቋምና ገቢዎቹን በመጠቀም፡፡
፫. ዩኒቨርሲቲው ዓላማውን በሚገባ ስለማሳካቱ በተለይም የሚከተሉትን ስለማረጋገጡ ተጠያቂነት ይኖርበታል፣
 ሀ) የሚያካሂዳቸው የትምህርትና የምርምር ፕሮግራሞች ከሀገሪቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር የተጣጣሙና ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቁ መሆናቸውን፣
 ለ) አጠቃላይ አሠራሩ ተቋማዊ ሆኖ በግልጽነትና በአሳታፊነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን፣

5. *Powers and Duties*

The University shall have the powers and duties to:

1/ establish faculties, colleges and other educational and research institutions and implement undergraduate and postgraduate programs;
2/ confer certificates, diplomas and degrees, and award academic titles and prizes to those who have made commendable contributions;
3/ undertake studies and research in priority areas for the development of the country;
4/ organize and conduct seminars, workshops and symposia;
5/ establish relations with local and foreign sister universities, research institutions, and other organizations having similar objectives;
6/ provide consultancy, special training and other appropriate services to the community, regional governments and the federal government;
7/ publish and distribute academic journals and newsletters;
8/ charge appropriate fees for the services it renders;
9/ establish and administer income fund and income generating enterprise;
10/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;
11/ carry out such other activities as are necessary for the attainment of its objectives.

6. *Academic Freedom, administrative Autonomy and Accountability*

1/ Subject to limitations provided by law, the University shall have academic freedom to search for, advance and disseminate knowledge.
2/ Subject to limitations provided by law, the University shall have administrative autonomy with respect to the following:
 (a) defining its internal organization and the administration of its budget and personnel;
 (b) curriculum review and development;
 (c) formulating research strategy and conducting same;
 (d) establishing relations with local and foreign institutions with a view to facilitating the discharge of its academic, research and community service duties;
 (e) Establishing income generating enterprise and using its proceeds.
3/ The University shall be accountable for the fulfillment of its objectives and, in particular, for ensuring that:
 (a) its educational and research programs are in line with the country's policies and strategies and meet international standards;
 (b) its activities are institutionalized, transparent and participatory;

ሐ) የበጀትና ሀብት አደላደሉና አጠቃቀሙ ወጪ ቆጣቢ መሆኑን፣

መ) ሠራተኞቹ በሚያስመዘግቡት የግልና የጋራ ውጤት የሚለኩ መሆኑን፣

ሠ) የተዋጣለት ተቋማዊ የትምህርትና የፋይናንስ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን፡፡

፯. <u>የመረጃ ልውውጥ</u>

ዩኒቨርሲቲው፣

፩. ቦርዱ በሚያጸድቀው የውስጥ ደንብ መሠረት ከግል ተቋማት፣ ከመንግሥታዊ ተቋማት እና ከሌሎች አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፤

፪. ማንኛውም ከትምህርት ጋር የተያያዘ ምርምር የሚሠራ ሠራተኛ ወይም ተማሪ ጥያቄ ሲያቀርብለት መረጃ ይሰጣል ወይም መረጃውን እንዲያገኝ ይረዳል፤

፫. የምርምርና ጥናት ጽሁፎች ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች፣ ተመራማሪዎችና ሌሎች ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል፤

፬. የወጪ መጋራት ውል ተጠቃሚ ተመራቂዎችን ዝርዝር ከተሟላ መረጃ ጋር ለሚኒስቴሩና ለፌዴራሉ አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በወቅቱ ያስተላልፋል፡፡

፰. <u>ጥናትና ምርምር</u>

፩. የጥናትና ምርምር ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘው አደረጃጀት በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ደንብና የአስተዳደር መዋቅር የሚወሰን ሆኖ በአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ይመራል፡፡

፪. ዩኒቨርሲቲው፣

ሀ) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምርምር ተቋማት ሊከፍት ይችላል፤

ለ) ለሚያከናውነው ምርምርና ጥናት በቂ ገንዘብ ማፈላለግ፣ መመደብና በሥራ ላይ ማዋል ይችላል፤

ሐ) ተመራማሪዎችንና የምርምር ረዳቶችን በግል ወይም በጋራ ቅጥር ሊያሰራ ይችላል፤

መ) ምርምሮችን አግባብነት ካላቸው ከሌሎች ተቋማት ጋር በትብብር ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፫. የዩኒቨርሲቲው የጥናትና ምርምር ርዕስ አመራረጥና አተገባበር፣ የበጀት አጠቃቀምና የሀብት አያያዝ የግልጽነትና የተጠያቂነት መርሆዎችን የተከተለ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለዩኒቨርሲቲው አስፈጻሚ አካላት

፱. <u>የዩኒቨርሲቲው ቦርድ</u>

፩. የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በሚኒስቴሩ የሚሰየም ሰብሳቢ እና የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ) የሚኒስቴሩ ተወካይ..............................አባል

ለ) በሚኒስቴሩ የሚሰየም የፌዴራል መንግሥት ተወካይ .......................................አባል

ሐ) ሦስት የክልሉ መንግሥት ተወካዮች.......አባላት

መ) በሚኒስቴሩ የሚሰየም አንድ ታዋቂ ግለ ሰብ..........................................አባል

(c) the allocation and utilization of its budget and resources are based on cost effectiveness;

(d) its personnel are evaluated on the basis of individual and collective results;

(e) it has successfully institutionalized its educational and financial information system.

*7. Information Exchange*

The University shall:

1/ exchange information with private and public institutions and other bodies in accordance with internal regulations approved by the Board;

2/ provide, upon request, a worker or a student who undertakes research relating to education with information or assist to have access thereto;

3/ make documents of research and studies available to students, researchers and other beneficiaries of the University;

4/ transfer, with relevant information and in due time, the list of graduating students who have benefited from cost sharing agreements to the Ministry and the Federal Inland Revenue Authority.

*8. Studies and Research*

1/ The structure necessary to conduct research work shall be determined by the internal regulations and organizational structure of the University and shall be led by the Academic and Research Vice President.

2/ The University may:

a) open research institutes when it finds necessary;

b) solicit, allocate and utilize sufficient fund for research and study it conducts;

c) engage researchers and their assistants on the basis of joint employment;

d) undertake research works in cooperation with other relevant organizations.

3/ The University's research and study project selection and implementation, budget utilization and resource ownership shall be governed by the principles of transparency and accountability.

## *PART THREE*
## *EXECUTIVE BODIES OF THE UNIVERSITY*

*9. The University Board*

1/ The University Board shall have a chairperson appointed by the Ministry and the following members:

(a) a representative of the Ministry...........Member

(b) a representative of the Federal Government designated by the Ministry ................Member

(c) three representatives of the Government of the Regional State .............................Members

(d) a renowned and meritorious person designated by the Ministry....................................Member

ሠ) ከባለድርሻዎች በቦርዱ የሚሰየሙ ሁለት ተወካዮች............................................አባላት
ረ) የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት..........አባልና ፀሐፊ

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሠ) መሠረት በቦርዱ የሚሰየሙ አባላት ለልማት አስተዋጽኦ ያደረጉና የዩኒቨርሲቲው አገልግሎት ተጠቃሚዎች መሆን አለባቸው።

፫. ቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ ፴፭ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

## ፲. የዩኒቨርሲቲው ሴኔት

ሴኔቱ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩. የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት............................ሰብሳቢ
፪. የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚዳንቶች.............አባላት
፫. የአካዳሚክ ፕሮግራም ኃላፊ.............................አባል
፬. የፋኩልቲ፣ ኢንስቲትዩት፣ የትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ዲኖች..............................................አባላት
፭. የህብረተሰብ አቀፍ የተግባር ትምህርት አስተባባሪ..................................................አባል
፮. የተከታታይና የርቀት ትምህርት ፕሮግራም አስተባባሪ......................................................አባል
፯. የሕዝብና የውጭ ግንኙነት ኃላፊ....................አባል
፰. የዩኒቨርሲቲው ሬጅስትራር............................አባል
፱. የተማሪዎች ዲን..............................................አባል
፲. ሁለት የአካዳሚክ ሠራተኞች ተወካዮች...........አባላት
፲፩. ሁለት የተማሪዎች ተወካዮች /ቢያንስ አንዷ ሴት/.....................................................አባላት
፲፪. የዩኒቨርሲቲው የሴቶች ጉዳይ ተወካይ............አባል
፲፫. የምርምርና ሕትመት ኃላፊ............................አባል
፲፬. በሴኔቱ የሚሰየሙ ተገቢነት ያላቸው ሌሎች ሰዎች........................................................አባላት

## ፲፩. የሴኔቱ ሥልጣንና ተግባር

በአዋጁ አንቀጽ ፴፯ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሴኔቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. በቦርዱ የሚወጡ አጠቃላይ መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፤
፪. የተማሪዎች አቀባበልን፣ የደረጃ አወሳሰንን፣ የዲስፕሊን ጉዳዮችንና ምረቃን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት፤ እነዚህኑ በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መመርመርና መወሰን፤
፫. አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥና ደረጃዎች አቅጣጫዎችን መወሰን፤
፬. ሕጎችንና በቦርዱ የሚወጡ ፖሊሲዎችን መሠረት በማድረግ የተማሪዎች አስተዳደርን፣ የትምህርት ነክ ጉዳዮችን፣ የትምህርት ኃላፊዎች አመራረጥን እና የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ዲሲፕሊንና ደመወዝ በሚመለከት መመሪያ ማውጣት፤
፭. የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማእረግ እንዲሰጥ ለቦርዱ ሃሳብ ማቅረብ፤
፮. የረዳትና የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ መስጠት፤
፯. የአካዳሚክ ሠራተኞን ቅጥር መመርመርና ማጽደቅ፤
፰. ፕሬዚዳንቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ መቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በየሩብ ዓመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ መሰብሰብ፤
፱. ተግባሩን ለሌሎች የዩኒቨርሲቲው አካላትና ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎች በውክልና ማስተላለፍ፤
፲. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን።

(e) two representatives of stakeholders designated by the Board .........................Members
(f) President of the University ..........Member and Secretary

2. Members designated by the Board pursuant to sub-article 1(e) of this Article shall have positive contributions to development and shall be beneficiaries of the services rendered by the University.
3. The powers and duties of the Board shall be as provided in Article 35 of the Proclamation.

## 10. *The University Senate*

The University Senate shall be accountable to the University President and shall have the following members:

1. President of the University...........Chairperson
2. Vice-Presidents of the University......Members
3. Academic Programs Officer..............Member
4. Deans of Faculties, Institutes, Schools and Colleges ...................................Members
5. Community Oriented Practical Education Coordinator..................................Member
6. Continuing and Distance Education Coordinator..................................Member
7. Public and External Relations Officer.......................................Member
8. Registrar of the University..................Member
9. Dean of Students ...........................Member
10. Two representatives of the academic Staff........................................Members
11. Two students' representatives (at least one female) .....................................Members
12. Gender Affairs Officer of the University...................................Member
13. Head of Research and Publication......Member
14. Other appropriate persons to be designated by the Senate..................................Members

## 11. *Powers and duties of the Senate*

Subject to the provisions of Article 37 of the Proclamation, the Senate shall have the powers and duties to:

1. implement directives issued by the Board;
2. set criteria for admission of students, determination of academic standards, disciplinary measures and graduation, and to examine and decide on petitions relating thereto;
3 determine general directions for conducting examinations and grading;
4. issue directives on the basis of laws and policies adopted by the Board, on student administration, academic matters, procedure for selection of academic heads and on employment, promotion, fringe benefits, discipline and salary of academic staff;
5. propose awarding of promotions of professorships to the Board;
6. award promotions of assistant and associate professorships;
7. examine and approve the employment of academic staff of the University;
8. without prejudice to the power of the President to call a meeting at any time where he deems it necessary, convene a meeting at least once every quarter;
9. delegate its duties to other bodies and standing or ad-hoc committees of University;
10. perform such other activities as may be assigned to it by the Board.

፲፪. ስለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች

፩. የዩኒቨርሲቲው ዕጩ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሆነው የሚቀርቡ ሰዎች የተመሰከረለት የአካዳሚክና የአስተዳደር ብቃት እንዲሁም መልካም ሥነ ምግባር ሊኖራቸው ይገባል።
፪. ዩኒቨርሲቲው ለፕሬዚዳንቱ ተጠሪ የሆኑ ሁለት ምክትል ፕሬዚዳንቶች ይኖሩታል።
፫. የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች አንድ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።
፬. የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በአዋጁ አንቀጽ ፵ የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፲፫. የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር

፩. የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክና ምርምር ምክትል ፕሬዚዳንት በአዋጁ አንቀጽ ፵፩ ከተደነገገው በተጨማሪ፤
 ሀ) በቦርዱና በሴኔቱ የተላለፉ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ በማዋል ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ ክፍሎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
 ለ) የዩኒቨርሲቲውን ፋኩልቲዎች ፣ ኮሌጆች ፣ ተቋሞች ፣ ትምህርት ቤቶች እና የተከታታይ ትምህርት ክፍሎችን ሥራ ያቅዳል፣ ይመራል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፤
 ሐ) የዩኒቨርሲቲውን የምርምርና ጥናት እንቅስቃሴዎችን ያቅዳል፣ ይመራል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፤
 መ) የዩኒቨርሲቲውን መጽሐፍት ቤት፣ ሬጅስትራር ጽሕፈት ቤትና ሌሎች በሥሩ ያሉትን ክፍሎች ይመራል፤ በበላይነት ይቆጣጠራል፤
 ሠ) ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችንና ትብብሮችን ያፈላልጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
 ረ) በስሩ ያሉ ክፍሎችን የሥራ አፈጻጸም፣ የበጀት ክፍፍልና አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ሪፖርት ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤
 ሰ) በቦርዱ፣ በሴኔቱና በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
፪. የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት፣
 ሀ) የዩኒቨርሲቲውን የአስተዳደርና የልማት ጉዳዮች በተመለከተ ፕሬዚዳንቱን ያማክራል፣ ይረዳል፤
 ለ) የተማሪዎች አገልግሎትን ፣ የፋይናንስን ፣ የአስተዳደርና የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲሁም ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
 ሐ) በቦርዱና በሴኔቱ የተሰጡ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል.፤
 መ) የዩኒቨርሲቲውን አስተዳደርና ማኔጅመንት አቅም ለማሻሻል ከብሔራዊና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል ፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል ፤
 ሠ) በስሩ ያሉ ክፍሎችን የሥራ አፈጻጸም ፣ የበጀት ክፍፍልና አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ሪፖርት ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል ፤
 ረ) የዩኒቨርሲቲውን ድርጅትና የቢዝነስ ክፍሎች በተመለከተ ያቅዳል፣ ይመራል ፣ ይቆጣጠራል፣ የሥራ ባህልን ያጎለብታል ፤

*12. President and Vice Presidents of the University*

1. The candidate President and Vice Presidents of the university shall have commendable academic and managerial ability and good conduct.
2. The University shall have two Vice Presidents who shall be accountable to the President.
3. The term of office of the President and Vice-Presidents of the University shall be five years.
4. The powers and duties of the President of the University shall be as provided in Article 40 of the Proclamation.

*13. Powers and duties of Vice Presidents*

1. The Academic and Research Vice-President of the University shall, in addition to the powers and duties stated in Article 41 of the Proclamation:
 a) implement decisions and directives of the Board and the Senate in directing and supervising the activities of organs of the University accountable to him;
 b) plan, direct and supervise the activities of faculties, colleges, institutes, schools and continuing education programs of the University;
 c) plan, direct and supervise research and studies activities of the University;
 d) direct and supervise the library, office of the registrar and other organs of the University which are directly accountable to him;
 e) solicit national and international links and partnerships, and follow their implementation;
 f) report to the President on the performance, budget allocation and utilization and other activities of the units under him;
 g) carry out other activities which may be specifically entrusted to him by the Board, the Senate and the President.
2. The Administration and Development Vice-President of the University shall:
 a) consult and assist the President with regard to the administrative and development activities of the University;
 b) direct and supervise the University students services, financial, administrative and support services as well as the activities of other organs of the University accountable to him;
 c) implement decisions and directives issued by the Board and the Senate;
 d) solicit and administer national and international partnerships to improve the administrative and management capacity of the University;
 e) report to the President on the performance, budget allocation and utilization and other activities of the units under him;
 f) plan, direct and supervise the Enterprise and business units of the University, and create an entrepreneurial culture;

ሰ) በዩኒቨርሲቲው አዳዲስ የቢዝነስ ሃሳቦችንና ልማትን ያቅዳል ፣

ሸ) የዩኒቨርሲቲውን አዳዲስ የልማትና የማስፋፋት የካፒታል ኢንቨስትመንቶችን ያቅዳል ያስተዳድራል፤

ቀ) ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የተገናኙና እርሱን የሚመለከቱ ስምምነቶችና ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይመራል ፣ ይቆጣጠራል ፤

በ) የቢዝነስና የስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ያቀርባል ፤

ተ) ሌሎች ከቦርዱ ፣ ከሴኔቱና ከፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፲፬. የአካዳሚክ ኮሚሽን

፩. እያንዳንዱ ፋኩልቲ ፣ ኮሌጅ ፣ ኢንስቲትዩት ወይም ትምህርት ቤት ለዲኑ ተጠሪ የሆነ የራሱ አካዳሚክ ኮሚሽን ይኖረዋል፡፡

፪. የአካዳሚክ ኮሚሽን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ) የፋኩልቲው፣ የኮሌጁ፣ የኢንስቲትዩቱ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲን...................... ሰብሳቢ

ለ) የፋኩልቲው፣ የኮሌጁ ፣ የኢንስቲትዩቱ ወይም ትምህርት ቤቱ ምክትል ዲኖች............ አባላት

ሐ) የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች.................. አባላት

መ) አንድ የተማሪዎች ተወካይ ................ አባል

ሠ) በአካዳሚክ ሠራተኞች ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ አንድ የመምህራን ተወካይ ................ አባል

ረ) የፋኩልቲው የተከታታይ ትምህርት አስተባባሪ............................................... አባል

ሰ) የፋኩልቲው ረዳት ሬጅስትራር ........... አባል

ሸ) በኮሚሽኑ የሚመደቡ አግባብነት ያላቸው ሌሎች ኃላፊዎች ...................አባላት

፫. የዩኒቨርሲቲው ሴኔት የሚያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ አካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፤

ሀ) የፋኩልቲውን ፣ የኮሌጁን ፣ የተቋሙን ወይም የትምህርት ቤቱን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በጀት በማዘጋጀት ይደለድላል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ለ) የሥልጠናና የትምህርት መርሀ ግብሮችን ሥርዓተ ትምህርቶች አዘጋጅቶ በሴኔቱ ያስጸድቃል፤

ሐ) በሴኔቱ መመሪያ መሠረት የተማሪዎችን ትምህርትና ሥነ-ምግባር የተመለከቱ ዝርዝር መስፈርቶችን ይወስናል ፤

መ) የክብር ዲግሪና ከትምህርት ጋር የተያያዙ ሽልማቶች እንዲሰጡ ለሴኔቱ ሃሳብ ያቀርባል ፤

ሠ) የሌክቸረር ፣ ረዳት ሌክቸረር ፣ ረዳት ምሩቅና የቴክኒክ ረዳቶችን ዕድገት በሴኔቱ መመሪያ መሰረት አጣርቶ ይወስናል ፤

ረ) የተባባሪና ረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለሴኔቱ ሃሳብ ያቀርባል፤

ሰ) የአካዳሚክ ሠራተኞች ቅጥርን ይመረምራል ፣ የነጻ ትምህርት ዕድልና የምርምርና ሳባቲካል ዕረፍቶችን ያጸድቃል ፤

ሸ) የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወስናል፤

ቀ) ከሴኔቱና ከፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ፡፡

g) plan, direct and supervise new ventures and development activities in the University;

h) plan and manage capital investments of the University that are related to new developments and expansions;

i) direct and supervise the implementation of agreements entered with other institutions and projects connected with activities falling within his mandates;

j) prepare and submit business and strategic plans;

k) carry out other activities which may be specifically entrusted to him by the Board, the Senate and the President.

## 14. *Academic Commission*

1. Each faculty, college, institute or school shall have an academic commission accountable to the dean.
2. The academic commission shall have the following members:
   (a) Dean of the Faculty, College, School or Institute................................Chairperson
   (b) Associate Deans of the Faculty, College, School or Institute......................Members
   (c) Heads of departments....................Members
   (d) A representative of students..............Member
   (e) A representative of the academic staff.........................................Member
   (f) Continuing education coordinator of the faculty.....................................Member
   (g) Associate registrar of the faculty........Member
   (h) Other appropriate officers to be designated by the academic commission..............Members
3. Subject to directives of the Senate, the academic commission shall have the powers and duties to:
   (a) plan activities of the faculty, college, institute or school and prepare and allocate budget, and follow up the implementation of same;
   (b) Prepare curricula of training and educational programs and submit same to the Senate for approval;
   (c) set educational and disciplinary standards of students in conformity with directives of the Senate;
   (d) recommend to the Senate the awarding of honorary degrees and education related prizes;
   (e) examine and decide, in accordance with directives of the Senate, on the awarding of academic promotions to the positions of lecturers, assistant lecturers, graduate assistants and technical assistants;
   (f) recommend to the Senate the awarding of the academic promotions of associate and assistant professorships;
   (g) examine the recruitment of the academic staff, and decide on cases of scholarships and research and sabbatical leaves;
   (h) adopt its own rules of procedures for conducting meetings;
   (i) perform other activities as may be assigned to it by the President and the Senate.

## ፲፭. የትምህርት ክፍል ጉባዔ

፩. እያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲው የትምህርት ክፍል የራሱ ጉባኤ ይኖረዋል ፡፡

፪. የትምህርት ክፍል ጉባዔ በትምህርት ክፍሉ ኃላፊ የሚመራ ሆኖ ሁሉንም የሙሉ ጊዜ መምህራንን ያካትታል ፡፡

፫. የትምህርት ክፍል ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

ሀ) በትምህርት ክፍሉ የሚሰጠውን ሰርቲፊኬት ፣ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ የሚያስገኙ መርሃ ግብሮችን ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ያቀርባል ፣ ሲፈቀድም ያስፈጽማል ፤

ለ) የትምህርት ክፍሉን ዓመታዊ ዕቅድ ፣ በጀትና ሪፖርት ያዘጋጃል ፤

ሐ) የትምህርት ክፍሉን የሰው ኃይልና ፋይናንስ አስተዳደር ይከታተላል ፤

መ) የመምህራንና የተማሪዎችን ክትትልና ግምገማ ያከናውናል ፣

ሠ) ፈተናዎችንና የአካዳሚክ ግምገማ ሥርዓትን ደረጃ ያወጣል፣ ይከታተላል ፤

ረ) የማስተማሪያ ጽሑፎችን አመራረጥና ዝግጅት ይወስናል ፣ የመምህራን የሥራ ጫናና ድልድል ይወስናል ፤

ሰ) በሥርዓተ ትምህርትና በመማር ማስተማር ሥርዓት ማሻሻያዎችና ፈጠራዎች እንዲጎለብቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሸ) የተማሪዎችን ውጤት ያጸድቃል ፤

ቀ) ሌሎች በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና በትምህርት ክፍሉ ኃላፊ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፲፮. ስለዩኒቨርሲቲው ልዩ ልዩ ክፍሎች የውስጥ አሠራር ነፃነት

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተዘረዘሩት የዩኒቨርሲቲው አካላት ድርጅታዊ መዋቅር በቦርዱ ይጸድቃል፡፡

፪. እያንዳንዱ ፋኩልቲ ፣ ተቋም፣ ትምህርት ቤት ወይም ኮሌጅ የበጀት ማዕከል ደረጃ ሊኖረው ይችላል ፡፡

፫. እያንዳንዱ የበጀት ማዕከል የራሱን ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ፣ የበጀትና ሀብት አጠቃቀምን ይወስናል፣ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል ፡፡

## ፲፯. ለአመራር ቦታዎች የሚጠየቁ መስፈርቶች

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉ አካላትን ለመምራት የሚታጭ ሰው በተለይ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፤

፩. የማኔጅመንት፣ አስተዳደርና የአመራር ብቃት ያለው፤

፪. በተቋሙ የአካዳሚክ፣ የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ውስጥ ብቁ ተሳትፎ ያለው፤

፫. ሥራዎቹ ውጤት ያሳዩና መልካም ሥነ-ምግባር ያለው፤

፬. ዲሞክራሲያዊ እሴቶችን የመተግበርና የማስረጽ ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ያለው፡፡

## 15. *Department Assembly*

1. Each department of the University shall have its own department assembly.
2. Every department assembly shall be composed of all fulltime academic staff members of the department and shall be chaired by the head of the department.
3. A department assembly shall have the powers and duties to:
   (a) submit recommendations to the academic commission on the programs of studies necessary for obtaining certificates, diplomas or degrees offered by the department , and implement same upon approval;
   (b) prepare the annual plan, budget and reports of the department;
   (c) monitor the financial and personnel management of the department;
   (d) conduct teachers' and students' appraisal and evaluation; examine complaints thereof;
   (e) standardize and supervise examination and academic evaluation systems;
   (f) determine teaching material selection and preparation to courses, and approve distribution of teaching load to staff members;
   (g) support and facilitate quality improve-ment and innovation in curriculum and learning teaching systems;
   (h) approve students' grades;
   (i) perform other activities assigned to it by the President of the University and head of the department.

## 16. *Internal Autonomy of Organs of the University*

1. The organizational structures of the various organs of the University referred to in sub-article (2) of Article 3 of these Regulations shall be approved by the Board.
2. Each faculty, institute, school or college may have a cost center status.
3. Each cost center shall prepare its own action plan and budget, decide on the utilization of budget and resources and prepare reports.

## 17. *Qualification Requirement for Leadership Posts*

A candidate nominated to serve as head of any organ of the University shall meet the following qualification requirements:

1. managerial, administrative and leadership competence;
2. demonstrated effective participation in the academic, research and community services of the University;
3. demonstrated results and good conduct;
4. preparedness and commitment to practice and inculcate democratic values.

## ክፍል አራት
## ስለዩኒቨርሲቲው ሠራተኞችና ተማሪዎች

፲፰. የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች

፩. ዩኒቨርሲቲው በአዋጁ የተመለከቱት ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፪. ዩኒቨርሲቲው ቦርዱ በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት የሌላ መንግሥታዊ ወይም የግል ተቋም ሠራተኛን በጋራ ቅጥር ማሠራት ይችላል።

፫. የጋራ ቅጥሩ በቅድሚያ የሌላው ቀጣሪ ፈቃደኛነት ተጠይቆ በዩኒቨርሲቲውና በግለሠቡ መካከል በሚደረግ ውለታ መሠረት ተግባራዊ ይሆናል ።

፬. በጋራ የተቀጠረው ባለሙያ እንደቋሚ መምህር የሚታይ ሆኖ በሕግ የተመለከቱ ግዴታና መብቶች ይኖሩታል።

፭. የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች መብትና ግዴታ በአዋጁ የተመለከተው ይሆናል።

፲፱. ስለተማሪዎች መቀበያ መመዘኛ

፩. በዚህ ደንብና በሌሎች ሕጎች ስለመቀበያ መመዘኛ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዩኒቨርሲቲው፣

ሀ) ተገቢውን መመዘኛ ላሟሉ ኢትዮጵያውያን ያለምንም ልዩነት ክፍት ይሆናል፤

ለ) የኢትዮጵያ የሁለተኛ ደረጃ የመዘጋጃ ትምህርት ወይም ሚኒስቴሩ በሰጠው ግምት ደረጃ ያለው የውጭ ሀገር ሁለተኛ ደረጃን ያጠናቀቀ እና የዩኒቨርሲቲውን የመግቢያ መመዘኛ ያሟላ ተማሪን ለቅድመ ምረቃ ዲግሪ መርሃ ግብር ትምህርት ይቀበላል፤

ሐ) የዲፕሎማ (12+2) ወይም (10+3) ደረጃ ያላቸው ተማሪዎችን በአድቫንስድ ተማሪነት በቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር ሊቀበል ይችላል፤

መ) የከፍተኛ ትምህርት የቅድመ ምረቃ ዲግሪ ትምህርት ያጠናቀቀና የዩኒቨርሲቲውን የመግቢያ መመዘኛዎችን ያሟላ ተማሪን ለድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር ትምህርት ይቀበላል፤

ሠ) ለሴቶች ፣ ለታዳጊ ክልል ብሔረሰብ እንዲሁም ለጎልማሳና ልምድ ላላቸው ተማሪዎች የትምህርት ሚኒስቴር በሚያወጣው የተለየ የአቀባባል ሥርዓት መሠረት ሊወስን ይችላል።

፪. ዩኒቨርሲቲው የሚቀበለው ተማሪ በወጪ መጋራት መርህ መሠረት ያለበትን ግዴታ የሚያሟላ መሆን አለበት።

፫. ዩኒቨርሲቲው የተማሪውን ችሎታና የዕውቀት ደረጃ እንዲሁም ክህሎት ለመገምገም የሚያስችል መመዘኛ ያዘጋጃል።

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጥ መመዘኛ ለተማሪው በተሰጠው ትምህርት ወይም ሥልጠና ይዘት ላይ የተመሠረተ ተከታታይ ምዘና መሆን አለበት።

፭. መመዘኛው የሚሰጥበት መንገድ በቃል ፣ በጽሑፍ ፣ በተግባርና ሌሎች ሴኔቱ በሚወስንባቸው መንገዶች ሊሆን ይችላል።

፮. ዩኒቨርሲቲው የምዘና ውጤቶችና የፈተና ወረቀቶችን ለተማሪው መመለስ ወይም በግልጽ ማሳወቅ አለበት።

## PART FOUR
## *STAFF AND STUDENTS OF THE UNIVERSITY*

18. *The University Staff*

1/ The University shall have staff as provided in the Proclamation.

2/ The University may, in accordance with directives of the Board, engage a staff of another government or private institution on the basis of joint employment.

3/ The joint employment shall be effected by concluding a contract between the University and the individual upon obtaining the prior consent of the other employer.

4/ The joint employee shall be considered as a full time academic staff and shall have the rights and obligations provided by law with respect to such staff.

5/ The University staff shall have the rights and obligations provided in the Proclamation.

19. *Admission of Students*

1/ Without prejudice to the provisions of these Regulations and other relevant laws regarding the requirements of admission of students, the University:

(a) shall be open to all qualified Ethiopians without any discrimination;

(b) shall admit, for undergraduate studies, students who have completed Ethiopian preparatory level school education or foreign high school education that has equivalent level as determined by the Ministry and satisfy its entrance qualification requirements;

(c) may admit students with diploma (12+2 or 10+3) as advanced students in its undergraduate programs;

(d) shall admit, for post graduate studies, students who have completed their undergraduate studies and satisfy its entrance qualification requirements;

(e) may determine according to Ministry of Education especial admission procedures for female students, students from developing regions, adults and experienced students.

2/ Any student admitted by the University shall be obliged to fulfill the requirements of principles of cost sharing.

3/ The University shall design an assessment mechanism that enables it to evaluate the ability and level of knowledge as well as skills of its students.

4/ The methods of assessment designed in accordance with sub-article (3) of this Article shall be based on the content of course or training offered to the student and based on continuous assessment.

5/ The methods of assessment may be oral, written, practical or any other form as determined by the Senate;

6/ The University shall return the results and examination papers to students or make a transparent notification of same.

## ክፍል አምስት
## ስለገቢ ማመንጫ ድርጅትና ገቢ ፈንድ

**፳. ስለድርጅቱ መቋቋምና አካላቱ**

ለዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ተጠሪ የሆነና የሚከተሉት አካላት ያሉት ድርጅት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፩. የምክር አገልግሎት፤
፪. የምርት አገልግሎት፤
፫. የፕሮጀክት አገልግሎት፤
፬. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ፤ እና
፭. በዩኒቨርሲቲው የሚቋቋሙ ሌሎች አገልግሎቶች ።

**፳፩. የድርጅቱ የገቢ ምንጭ**

በአዋጁ የተደነገጉት የድርጅቱ የገቢ ምንጮች እንደተጠበቁ ሆኖ፣

፩. ይህ ደንብ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከዩኒቨርሲቲው የገቢ ምንጭ አካላት የተገኙ ገቢዎች የድርጅቱ ገቢዎች ይሆናሉ፤
፪. ደንቡ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የነበሩ የዩኒቨርሲቲው የገቢ ማመንጫ ክፍሎች በድርጅቱ ሥር ይሆናሉ።

**፳፪. ድርጅቱ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች**

ፈቃድ ማግኘትን የመሳሰሉ በሕግ የተደነገጉ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ድርጅቱ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ሊሰጥ ይችላል፤

፩. የማማከርና የሥልጠና አገልግሎት፤
፪. የምርትና የቴክኒክ አገልግሎት፤
፫. የፕሮጀክት ጥናት አገልግሎት፤
፬. የኢንተርኔት ካፌና የኮምፒውተር አገልግሎት፤
፭. የመሳሪያዎችና መገልገያዎች ኪራይ አገልግሎት፤
፮. የመጻሕፍትና የሕትመት ውጤቶች ሽያጭ አገልግሎት።

**፳፫. የድርጅቱ አመራር**

የድርጅቱ አመራር አጠቃላይ ፖሊሲ፣ የድርጅቱ መዋቅር፣ ካፒታሉ፣ ድርጅቱንና አካላቱን የሚመሩ ሰዎች አመራረጥና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮች በቦርዱ ይወሰናሉ።

**፳፬. የድርጅቱን የፋይናንስ መግለጫና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ስለማቅረብ**

የድርጅቱ የፋይናንስ መግለጫና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት የድርጅቱ የበጀት ዓመት ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት የሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ መቅረብ አለበት።

**፳፭. ስለፈንድ መቋቋም**

ዓላማና የገቢ ምንጩ በአዋጁ የተገለጸው የዩኒቨርሲቲው ፈንድ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

**፳፮. የፈንዱ አካላት**

፩. ፈንዱ፣
  ሀ) የፈንዱ አስተዳደር ቦርድ (ከዚህ በኋላ «የፈንዱ ቦርድ» ተብሎ የሚጠራ)፣ እና
  ለ) ሴክሬታሪያት፣ ይኖረዋል፤
፪. የፈንዱ ቦርድ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ይሆናል።

**፳፯. የፈንዱ ቦርድ አባላት**

፩. ቦርዱ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።
፪. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።
፫. የቦርድ አባል በማናቸውም ምክንያት ሥራውን መሥራት ካልቻለ በምትኩ አዲስ አባል ይሰየማል።

## PART FIVE
## *INCOME GENERATING ENTERPRISE AND FUND*

20. *Establishment of the Enterprise and its Units*

An enterprise, accountable to the University Administration and Development Vice-President , having the following units is hereby established:

1/ the consultancy service;
2/ the production service;
3/ the project service;
4/ the information technology service; and
5/ other services to be established by the University.

21. *Source of Income*

Without prejudice to the income sources of the Enterprise provided by the Proclamation:

1/ income generated from income generating units of the University before the coming into effect of these Regulations shall be income of the Enterprise;

2/ income generating units of the University established before the coming into force of these Regulations shall be under the Enterprise.

22. *Power and Duties of the Enterprise*

Without prejudice to legal requirements such as acquiring licenses, the enterprise may engage in rendering:

1/ consultancy and training services:
2/ production and technical support services;
3/ project study services;
5/ leasing services of equipment and facilities;
6/ sales services of books and other publications.

23. *Management of the Enterprise*

The general management policy, structure and capital of the enterprise, the selection of managers of the enterprise and its units and other relevant issues shall be determined by the Board.

24. *Submission of Financial and Activity Reports of the Enterprise*

The financial and activity reports of the Enterprise shall, within three months after the end of its fiscal year, be submitted to the Board.

25. *Establishment of the Fund*

A Fund is hereby established for the purpose and having source of income as provided by the Proclamation.

26. *Organs of the Fund*

1/ The Fund shall have:
  (a) an administrative board (hereinafter the "Fund Board"); and
  (b) a secretariat.
2/ The Fund Board shall be accountable to the President of the University.

27. *Members of the Fund Board*

1/ Members of the Fund Board shall be designated by the President of the University.
2/ The term of office of members of the Fund Board shall be two years.
3/ A new member shall be appointed to replace any member of the Fund Board who, for any reason, is unable to discharge his duties.

፳፰. <u>የፈንዱ ቦርድ ሥልጣንና ተግባር</u>

የፈንዱ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የፈንዱ ገቢዎች በሚገባ መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፤
፪. ፈንዱ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፤
፫. በሴክሬታሪያቱ የሚቀርብለትን የፈንዱን ሪፖርት መርምሮ ያጸድቃል፤
፬. ለፈንዱ ዓላማ መሳካት የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፳፱. <u>የፈንዱ ቦርድ ስብሰባዎች</u>

የፈንዱ ቦርድ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

፴. <u>የሴክሬታሪያቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. ዓመታዊ በጀት እንዲሁም የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ መግለጫ ሪፖርቶችን ለፈንዱ ቦርድ አቅርቦ ያስጸድቃል፤
፪. በፈንዱ ድጋፍ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችን ይመረምራል፣ በፈንዱ ቦርድ መመሪያ መሠረት የፕሮጀክቶቹን የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ይፈቅዳል፤
፫. ለፈንዱ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን ያጠናል፤
፬. የፈንዱ ቦርድ ውሳኔዎች በትክክል መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤ የቦርዱን የሥራ መዛግብት፣ ዘገባዎ ችንና የስብሰባ ቃለ ጉባዔዎች ይይዛል፡፡
፭. በፈንዱ ቦርድ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

፴፩. <u>የፈንዱ ሴክሬታሪያት ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>

የፈንዱ ሴክሬታሪያት ዳይሬክተር ፈንዱን በሚመ ለከቱ ጉዳዮች ተጠሪነቱ ለፈንዱ ቦርድ ሆኖ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴ የተመለከቱትን የሴክሬታሪያቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፴፪. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

፴፫. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

ዲላ የመምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በመባል የሚታወቀው ተቋም መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለዩኒቨርሲቲው ተላልፈዋል፡፡

፴፬. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

28. *Powers and Duties of the Fund Board*

The Fund Board shall have the powers and duties to:

1/ ensure that the incomes of the Fund are duly collected;
2/ ensure that the Fund is utilized for the intended purposes and issue the necessary directives for the execution of same;
3/ examine and approve the reports submitted by the Secretariat on the application of the Fund's income;
4/ carry out other activities necessary for the achievement of the objectives of the Fund.

29. *Meetings of the Fund Board*

The Fund Board shall adopt its own rules of procedure for conducting meetings.

30. *Powers and Duties of the Secretariat*

The Secretariat shall have the powers and duties to:

1/ prepare and submit to the Fund Board, for its approval, annual budgets and activity and financial reports of the Fund;
2/ examine projects financed by the Fund, and allocate, in accordance with directives of the Fund Board, operational budget for the implementation of same;
3/ undertake studies to identify additional sources of income for the Fund;
4/ ensure the proper implementation of decisions of the Fund Board and keep its working documents, reports and minutes;
5 / perform other activities assigned to it by the Fund Board.

31. *Powers and Duties of Director of the Secretariat of the Fund*

The Director of the Secretariat of the Fund shall be accountable to the Fund Board with respect to matters related to the Fund, and shall exercise the powers and duties of the Secretariat provided for under Article 30 of these Regulations.

## PART SIX
## *MISCELLANEOUS PROVISIONS*

32. *Inapplicable Laws*

No regulation or directive shall, in so far as it is inconsistent with the provisions of these Regulations, be applicable with respect to matters provided for by these Regulations.

33. *Transfer of Rights and Obligations*

The rights and obligations of the institution known as the Dilla College of Teachers' Education and Health Sciences are hereby transferred to the University.

34. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of December, 2006.

MELES ZENAWI

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC RREPUBLIC OF ETHIOPIA*